# መልካም ገና ይሁንላችሁ! እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የጾምና የጸሎት ፕሮግራም

በቤተ ክርስቲያን የታወጀው የጾምና የጸሎት ፕሮግራም በDecember 26, 27, እና 28 ከሰአት ከ12፡30 ጀምሮ እስከ 3፡00 ድረስ እንዲሁም በDec. 29 (አርብ) በመደበኛ ፕሮግራማችን ጊዜ ይካሄዳል። በዚህ የጾም ጸሎት ፕሮግራም የምንችል ሁሉ እንድንካፈል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

### የአዲስ አመት ፕሮግራም

የችካጎና አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት በብረሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን በአንድነት ማዕድ በመቁረስ፣ በጸሎት፣ በአምልኮ፣ ቃሉን በመካፈልና በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የአዲስ አመት ማዜማ ፕሮግራምን በጋራ ያካሂዳሉ። ሁላችንም በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንሁን።

### የሕንጻ ፈንድ ማሰባሰብ ፕሮግራም

ለሕንጻ ግዢ ለመስጠት ቃል የገባነውን ገንዘብ በገባችሁት ቃል መሰረት የፈጸማችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ለመስጠት ቃል የገባችሁ ደግም ስጦታውን እስከ አመቱ መጨረሻ (ወይንም ቃል በገባነው መሰረት) እንድንሰጥ እናበረታታችኋለን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኝት፡-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

## መልካም የገና በዓል ይሁንልን። የበዓሉ ምክንያት ኢየሱስ ነው።

For unto us a CHILD is born, unto us a Son is given, and the Government shall be upon His shoulders, and His Name shall be called, Wonderful, Counselor, Mighty God, Everlasting Father, Prince of Peace!
Isaiah 9:6

"ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና..."
(ኢሳ. 9፡6)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625


መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.


**December 24, 2017** — **ታኅሣስ 15፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር፡ ልዩ የገና ፕሮግራም

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ልዩ የገና ፕሮግራም ............. | የልጆች አገልግሎት ክፍል |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።”

(ኢሳ. 9፡6)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኀ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና

*“ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።” (ኢሳ. 9፡6)*

ከብዙ መቶ አመታት በፊት ነብዩ ኢሳያስ በመንፈስ ተነድቶ ይህንን ታላቅ ትንቢት ተናገረ። ትንቢቱም በኢየሱስ መወለድ ተፈጸመ። የኢየሱስ መወለድ የፍጥረትን አቅጣጫ የቀየረ ነው። ሕጻን ሆኖ የተወለደው ኢየሱስ “መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ የሆነ ጌታ” ቢሆንም ምድር ልታስተናግደው ስፍራ አልነበራትምና “በግርግም” ተኛ። ነገር ግን በዚያው ቅጽበት ሰማይ እየተደነቀ በዝማሬ ያሸበሸብ ነበር። ብስራቱ አስቀድም ለነገስታት ሳይሆን በሜዳ ላደሩ እረኞች ደረሰ። የምስራች ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት፣ ክርስቶስ ጌታ ተወልዷል የሚል ብስራት ከሰማይ መጣ። ታላቅ የሰማይ ሰራዊት በዝማሬ እግዚአብሔርን አመሰገኑ — ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድር፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ። ምድር ያልተቀበለችው ሰማያትን ያስደነቀ ልደት።

ሲወለድ ሰማያት ምልክትን ሰጡ። ሰባ ሰገል ከምስራቅ ኮኮቡን አይተው ሊሰግዱለት መጡ። ንጉስ እንደተወለደ ተረድተው በምሪት መጥተው ወድቀው ሰገዱለት። የከበረ ስጦታቸውንም በፊቱ አቀረቡ። ነገስታት ግን ደነገጡ፣ ፈሩ። እርሱን ለመግደል አስበው የቤተ ልሔምን ሕጻናት ፈጁ። እነ ሄሮድስ የተወለደው “ሕጻን” በስጋ የተገለጠ መለኮት እንደሆነ አልተረዱም። ዮሐንስ ስጋ የሆነው መለኮት ነው ሲል አወጀ። ማቴዎስ የተሰጠን ወንድ ልጅ ሕዝቡን ከኃጢያት የሚያድን እንደሆነ አበሰረ። ለሰው ልጅ የእግዚአብሔርን አብሮነት የሚመልስ — ሰው የጎደለው ክብር የሚመለስበት፤ እግዚአብሔር እንደገና ከሰው ጋር የሚሆንበት የእግዚአብሔር ውድ ስጦታ እንደሆነ ተናገረ። ዮሐንስ እርሱ በጸጋ ላይ ጸጋ ተሞልቶ እንደመጣ አወጀ። በመካከላችንም ያደረው ከሙላቱ ሊያካፍለን እንደሆነ ሰበከ። ነብዩ ኢሳያስ እግዚአብሔር ሕጻን ሆኖ ወደ ምድር የመጣውን አንድ ልጁን እንደሰጠን ወንጌልን አስቀድም በትንቢት ተናገረ። ሕጻን ሆኖ መጥቶ በመካከላችን ያደረው ኢየሱስ አለቅነትን በጫንቃው ላይ የተሸከመ ነው። የምድር ሁሉ ፈጣሪ የሆነ ኃያል አምላክ ነው። የተፈጠረው አለም ሁሉ በእርሱ ተፈጥሯል፤ አሁንም ጸንቶ ያለው በርሱ የስልጣን ቃል ተደግፎ ነው። የተወለደው ንጉስ ድንቅ መካር ነው። ነፍስን የሚያድን ምክር በርሱ ዘንድ አለ። የአባትነት ሁሉ ምንጭ የሆነ የዘላለም አምላክ ነው። ለተቀበሉትና ላመኑት ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅነትን ስልጣን ያጎናጽፋል። የሰላም ሁሉ ምንጭ የሰላም አለቃ ነው። አለም የማትሰጠውን ሰላም ይሰጣል። መልካም ገና!